# ብሄራዊ ክህደት

ከዙዋይ ረዚን፣ ጄኔቫ

የነገድ በሽታ የእምነት ግጭት
ታሪክን ማሸርሞጥ ያላንዳች ሃፍረት
ከውስጥ እየናዱ ያገር መሰረት
ወገን ትመሥሎ ሊያጠፋን የመጣ
ሻቢያ ወያኔ ነው የኢትዮጵያ ባላንጣ
ዋኖቹ እኚህ ናቸው የአገራችን ጣጣ
ስሙ ኢትዮጵያውያን፤

ለወያኔ ተንኮል ባትጠነቀቁ
የአገርን ክብር ለባንዳ ብትለቁ
ካልተባበራችሁ ገበሬና ሊቁ
ቶሎ ካልተፈታ የከሀዲ ትጥቁ
ችላ ማለት ወንጀል መሆኑን ዕወቁ!

በወያኔ ሥራ ተንኮል የተነሣ
ተከምሮ ታዬ የንፁሓን ሬሣ
የኢትዮጵያ ሰማይ ድንገት ተለወጠ
የወያኔ መንጋ የአገር ክብር ረገጠ
በወያኔ ስብከት እየተገበዘ
ያገር ልጅ መጣላት መተራረድ ያዘ
ማስተዋል ተሥኖት በመንፈስ ታረዘ!
ሕፃናት ማቃጠል በሚፋጀው ረመጥ
በአረመኔ ተግባር የሴትን ጡት መቁረጥ
በጥፋት መደሰት የነገድ ድብደባ
ከወያኔ ጋራ እረ ገደል ይግባ
ድራሹ እልም ይበል ይውጣ ብትንትኑ
የሻቢያ ጭቃሹም ወያኔ ጭፍኑ
እሱና ጌቶቹ በጥብቅ ይኮነኑ!
እፍኝ በማይሞላ የወያኔ መንጋ
ይኸማ የጉድ ነው አገር ከተናጋ
ሲዘረፍ ጭጭ ካልን ያገራችን ፀጋ
ማለት ነው አልገባንም ብሄራዊ ዋጋ
በኮሄን ዕርዳት ወያኔ ሲገባ
ከሐውዜን እንሥቶ እስካዲስ አበባ
መጀመሪያ የወጣው ሕገወጥ አዋጁ
አፍ አውጥቶ ብሏል ሰዎችን ተፋጁ
“ኤርትራ ትገንጠል ትሂድ ኡጋዴን”
ይርዘም በማታለል የወያኔ ቀን
ከሕዝብ በላይ ሆኖ መለሰ ይጀነን
ታምራት ነው ምስክር በባንዳ ሥልጣን
ጥዋትና ማታ የወያኔ ጉራ
ዴሞክራሲ አመጣን በዲክታተር ሥፍራ
በራስ መወሰን ነው የራስን ዕድል
ነገድን ማዋጋት መገነጣጠል
ድንቁርናን መቁጠር እንደዕውቀት ገድል
ሐሰትን ማራባት ማንቋሸሽ እውነት
እምነት ክህደት ሲሆን ክህደትም እምነት
መፎከሪያ ሆነ በወያኔ ቤት!
“አፎቱን ይቀዳል እምብዛም ስለት
ከመሞት ያደርሣል አይንአውጣ ብልጠት”
ተብሎ አልቆለታል ጥንትም ሲተረት
የወያኔ ክህደት ቢከመር ቢበዛ
የኢትዮጵያ አንድነት አይፈርስም በዋዛ
በኢትዮጵያ የደረሰው የዛሬው መከራ
የበቀል ውጤት ነው የጥፋት አዝመራ
አገርን ለመሸጥ ምለው ለተነሱ
የኢትዮጵያን ጥራት የሚያደፈርሱ
ያላንዳች ማመንታት ወያኔን ክሰሱ
ስል እንዴ የሚያቅተው አይቶ መለየት
የወያኔን ሴራ የአገር ክህደት
እንኳን ሊከተለው እንኳን ሊያምንበት
ትኋንን ጌጥ ብሎ የሚሰግድለት?
ከአቶ ጂሎ በቀር አድርባይ ሆዳሙ
ከዶሮ የማይሻል የረከሰ ደሙ!
አገር አፍቃሪዎች ያለማመንታት
በፍጥነት አድርሱ ይህንን መልዕክት
ለኢትዮጵያ ሕዝብ በጊዜ አስተምሩ
ጀሮ ላለው ሁሉ ለቅን ሰው ንገሩ
“ዋጋቢስ ይሆናል የሕይወት ዓላማ
አንድነት ከሌለ ሕዝብ ካልተስማማ
ተቃጥሎ ይጠፋል ገጠርም ከተማ”
የማሰብ ድህነት የጥጋብ ድንፋታ
የቅሌታም መዝሙር የደንቆሮ ሐተታ
ወያኔ የሚረጨው መሠሪ አሉባልታ
በነቃ ሕዝብ ዘንድ አይኖረውም ቦታ
ሕገ ወጥ መንግሥት የአስተዳደር ዙኬ
ኢትዮጵያ አትፈልግም አጉል ዝባዝንኬ!

ያለበለዚያ በከንቱ ቸል ካልን
በከንቱ እንጠፋለን
አገር ትፈርሣለች
ታሪካችን ሳይቀር
ተፍቃ ታርፋለች
እንደቀላል ነገር

በስምንተኛው ሺ ብልጥ በዓለም ሞልቶ
ወያኔ የሚያታልለው ማንን ይሆን ከቶ
ካቶ ጅሎ በቀር ከበጉ ከከብቱ
ማደሪያ የሚፈልግ ላአድርባይነቱ!

---

TPLF and EPLF cannot be reformed, like apartheid, they should be abolished !